በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 234499

ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡...**

1. እትመት አሠፋ
2. ደጀኔ አያንሳ
3. ብርቅነሽ እሱባለው
4. ሀብታሙ እርቅይሁን
5. ብርሃኑ መንግስቱ
6.

**አመልካች፡-** የደንበጫ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት

**ተጠሪ፡-** አቶ መንበሩ ካሴ

ለምርመራ የተቀጠረውን መዝገብ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 113071 ሰኔ 17 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሥር ፍርድ ቤቶች ከተጠሪ ላይ ለልማት ለተወሰደው የከተማ ይዞታ የሥር ተከሳሽ ትክ ቦታ ሊሰጣቸው ይግባል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላልተገኘበት የሰበር ቅሬታው ለሰበር ሰሚው ችሎት አያስቀርብም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ሰሚው ችሎት ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ነሃሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በልማት ምክንያት ለተወሰደ መሬት የምትክ ቦታ እና የካሣ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደንበጫ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው ፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ተጠሪ ከሳሽ ፣ የደንበጫ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ኮንስትራክሽንና ከተማ ልማት አገልግሎት ጽ/ቤት ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የሟች አባቴ አቶ ካሴ ጥሩነህ በደንበጫ ከተማ 01 ቀበሌ በምሥራቅ ካሴ ጥሩነህ ፣ በምዕራብ ኃይሌ ምትኬ ፣ በደቡብ እማሆይ ሙልዬ ዘሪሁን እና በሰሜን ዋና መንገድ የሚያዋስነው 250 ካ.ሜ ፤ እንዲሁም በዚሁ ቀበሌ በምሥራቅ ቀጭን መንገድ ፣ በምዕራብ እማሆይ ሙልዬ ዘሪሁን ፣ በደቡብ የእግር መንገድ እና በሰሜን ካሴ ጥሩነህ የሚያዋስነው 250 ካ.ሜ የሆነ የድርጅት ቦታ ፣ የመጨረሻ በዚሁ ቀበሌ በምሥራቅ መንገድ ፣ በምዕራብ በሊዝ የተሸጠ ቦታ ፣ በሰሜን የስንታየሁ ቤት እና በደቡብ መንገድ የሚያዋስነው 250 ካ.ሜ አንደኛ የድርጅት ቦታ የሥር ተከሳሽ ምንም ዓይነት ትክ ቦታ ሳይሰጠኝ ስለወሰደ በ1ኛ እና 2ኛ ተራቁጥር ለተጠቀሱ ቦታዎች ትክ ቦታ እንዲሰጠኝ ፤ እንዲሁም በ3ኛ ተራቁጥር የተጠቀሰውን ቦታ ደግሞ ሊዙን ሰርዞ ቦታውን ያስረክበኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሥር ተከሳሽም በቁጥር ደም/አ/ህ/07/03/13 በተፃፈ ምላሽ ክስ የቀረበባቸው መሬቶች የህዝብ እና የመንግስት በመሆኑና በሕጋዊ መንገድ ለሶስተኛ ወገን የተላለፉ በመሆኑና የከሳሽ ጥያቄ የሕግ መሠረት ስለሌለው ውድቅ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ፣ የማጣሪያ ምስክር ስምቶ ፤ እንዲሁም የሟች የተጠሪ አባት ፋይል አስቀርቦ መዝገቡን እንደመረመረው፡- ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት አካለት አከራካሪው ይዞታ የማን እንደሆነ አጣርተው እንዲልኩ በተደጋጋም ብታዘዝም ውጤት ባለመቅረቡ የምስክሮች ቃል ላይ ተመስርቶ ጉዳዩን መመርመሩን ገልጾ ፤ የሥር ተከሳሽ ምስክሮች አከራካሪው መሬቶች ከመሰረቱ የማን እንደሆኑ እንደማያውቁና ቦታዎቹ ለአገልግሎት ሲውሉ ተቃውሞ ያልነበረ መሆኑን ፤ እንደዚሁም ቦታዎቹ የሟች የተጠሪ አባት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩን መስክረዋል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ደግሞ መሬቱ ቀድሞ የሟች ቤት የነበረበት ሲሆን በ2006 ዓ.ም በህገ - ወጥ መንገድ የተወሰዱ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ የማጣሪያ ምስክሮችም ቦታዎቹ የተጠሪ አያት የእርሻ መሬቶች ናቸው ሲሉ መስክረዋል፡፡ የሟች የአቶ ካሴ ጥሩነህ ፋይል ስመረመር በምስራቅ ቂስ ፈቃዴ ሽፈራው ፣ በምዕራብ ክፍት ቦታ ፣ በሰሜን ዋና መንገድ እና በደቡብ ካሴ ጥሩነህ የሚዋሰነው ቦታ ጀርባ የፈረስ ቤት የነበረ መሆኑን በቁጥር 123.679 ሐምሌ 23 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ ከፋይሉ ጋር ተያይዟል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ከተከሳሽ ምስክሮች በተሻለ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መልኩ በክሱ 2ኛ እና 3ኛ ተራቁጥር ላይ የተጠቀሱ ቦታዎች የሟች የተጠሪ ወላጅ አባት የነበሩ መሆኑንና ምንም ዓይነት ትክ ቦታ ሳይሰጥ እንደተወሰደባቸው አስረድተዋል፡፡ ተጠሪ ለተወሰዱባቸው በደንበጫ ከተማ 01 ቀበሌ በተለምዶ ዶክተር አእምሮ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ በምሥራቅ መንገድ ፣ በምዕራብ እማሆይ ሙልዬ ዘርሁን ፣ በሰሜን ካሴ ጥሩነህ እና በደቡብ የእግር መንገድ የሚያዋስነው 250 ካ.ሜ ፤ እንዲሁም በዚሁ ቀበሌ በምሥራቅ መንገድ ፣ በምዕራብ በሊዝ የተሸጠ ይዞታ፣ በሰሜን የስታየሁ ቤት እና በደቡብ መንገድ የሚያዋስነው 250 ካ.ሜ ቦታ ትክ ሳይሰጥ የሥር ተከሳሽ ወስዶ ለከተማ አገልግሎት ስላዋላቸው ትክ ቦታ ሊሰጥ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ ውሳኔውን በመቃወም ያቀረበው የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በየደረጃው ባሉ ጉዳዩን በተመለከቱ የሥር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በሥር የደንበጫ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረውን የደንበጫ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት በወረዳው ፍትሕ ጽ/ቤት ተወክሎ መከራካሩን በመግልጽ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- መንግስት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የከተማ ቦታዎችን በሚያስለቅቅበት ጊዜ ትክ ቦታ አልተሰጠኝም ካሣ አልተከፈለኝም የሚል ጥያቄ በመጀመሪያ ሊቀርብ የሚገባው ለከተማ የይዞታ አጣሪ እና ካሣ ገማች ኮሚቴ እንጅ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ስላልሆነ የደንበጫ ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ የመወሰን የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ሳይኖረው ጉዳዩን ማየቱ ስህተት ሆኖ እያለ ስህተቱ በበላይ ፍርድ ቤቶች አለመታረሙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ አከራካሪዎቹ ቦታዎች የተጠሪ አባት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አግባብነት ያለው የሰነድ ማስረጃ ስላልቀረበ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የለውም በማለት በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ ታልፎ በፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ መሰጠቱ አግባብነት የለውም፡፡ ክርክሩን ለማስረዳት አግባብነት ያለው ካርታና ፕላን ባልቀረበበት የተጠሪ የሥጋ ዘመድ የሆኑት ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመስማት ፤ እንዲሁም ያለሥልጣኑ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ቦታዎቹ የአቶ ካሴ ጥሩነህ ናቸው በማለት የሰጠውን ማስረጃ መሰረት አድርጎ መወሰኑ የማስረጃ ምዘናው ስህተት ያለበት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪ የውርስ ሃብቱን በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ስላልጠየቀ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

የሰበር አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆኑት ከወላጅ አባታቸው በውርስ ያገኙት ይዞታ መሬቶች በአመልካች ስለተወሰዱባቸው ትክ ቦታ እንዲሰጣቸው ያቀረቡትን ክስ የሥር ፍርድ ቤት ተበቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን፤እንዲሁም ስለይዞታው ከሚመለከተው የመንግስት አካል ሳይጣራ በሰው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ የተወሰነበትን አግባብ ለመመርመር መዝገቡ ለሰበር ሰሚው ችሎት እንድቀርብ እና ተጠሪም በጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ፡- በሥር ፍርድ ቤት ክርክር ያደረጉት ከደንበጫ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ኮንስትራክሽን ከተማ ልማት አገልግሎት ጽ/ቤት ጋር ሆኖእያለ የደንበጫ ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በሥር ፍርድ ቤት ከተጠሪ ጋር ተከራካሪ ባልሆነበት የሰበር ቅሬታ አቅራቢ ሊሆን የሚችልበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሕግ አግባብ ባለመኖሩ በቂ ኪሳራ ጋር መዝገቡ እንዲዘጋልኝ እጠይቃለሁኝ። ያለ ምንም የካሣ ክፍያ ፤ እንዲሁም ትክ መሬት ሳይሰጥ የተወሰደን መሬት የሚመለከቱ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች የማየት ሥልጣን አላቸው። በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29 መሠረት አቤቱታ ለማቅረብ አስቀድሞ የተሰጠ የካሣ ግምት ወይንም ትክ ቦታ ውሳኔ መኖር አለበት።። ያለ ምንም ከሣ ክፍያ እና ትክ ቦታ ሳይሰጥ ከይዞታ ላይ መፈናቀልን ተጠቃሹ ሕግም ሆነ ድንጋጌ አይመለክትም። ከይዞታዬ ያለአግባብ ስለተፈናቀልኩኝ መብቴ ለማስከበር ያቀረብከትን ክስ ፍርድ ቤቱ አይቶ ውሳኔ መስጠቱ የሚያስነቅፍ አይደለም። አከራካሪውን ይዞታ በሚመለከት አጣርተው እንዲያቀርቡ ለሚመለከከታቸው የመንግስት ተቋማት ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ብሰጥም አጣርተው ውጤት ለመላክ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ምስክሮች ተሰምቶ እና ፋይሉ ታይቶ ውሳኔ መሰጠቱ ተገቢ ነው። አከራካሪው መሬት ከይዞታችን ወጥቶ ስለማያውቅ እና በ2006 ዓ.ም በሕገ - ወጥ መንገድ እንደተወሰደብኝ በምስክሮች ስለተረጋገጠ የቀረበው ክስ በይርጋ አይታገድም። የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የስር ፍርድ ቤት አከራካሪው ይዞታ የአውራሼ መሆኑን አረጋግጦ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም። ከላይ በተመለከቱ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቶ በቂ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፊ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከመመርመሩ በፊት የሰበር አቤቱታው የቀረበው ገዳዩ በሚመለከተው ሰው መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዞ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የሰበር ሥርዓት የተዘረጋው ፍርድ ቤቶች እራሳቸውን በራሳቸው መቆጣጠር እንዲችሉ ፤ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ፍርድ ፀንቶ እንዳይቆይ ለማድረግ ፤ ተመሳሳይ ገዳዮች በተመሳሳይ ሁኔታ ተተርጉሞ ወጥ የሕግ አተገባበር ሥርዓት እንዲኖር ማስቻልን ዓላማ እና ግብ አድርጎ መሆኑ ይታመናል። አንድ ጉዳይ በሰበር ለመታየት ብቁ ለመሆን በመጀመሪያ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይንም ሌሎች የዳኝነት ሥልጣን በሕግ በተሰጣቸው አካላት ዘንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አቤቱታ አቅራቢውም በሥር በነበረው ክርክር ተካፋይ የነበረ ክርክሩም የሚመለከተው የይግባኝ ደረጃውን ያጠናቀቀ መሆን አለበት። የሰበር አቤቱታን የሚያቀርበው "የሚመለከተው አቤት ባይ" (concerned applicant) መሆን እንዳለበት የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 27(2) ይደነግጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሥር ፍርድ ቤቶች ተከራካሪዎች የነበሩት ተጠሪ እና የደንበጫ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ኮንስትራክሽን ከተማ ልማት አገልግሎት ጽ/ቤት መሆኑን መዝገቡ የሚያመለክት ከመሆኑም በላይ በደንበጫ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረው የደንበጫ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት በወረዳው ፍትሕ ጽ/ቤት ተወክሎ መከራካሩን የደንበጫ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የሚያመለክት ሲሆን ፤ ተጠሪም ለሰበር አቤቱታ በሰጡት ምላሽ በሥር ፍርድ ቤት ክርክር ያደረጉት ከደንበጫ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ኮንስትራክሽን ከተማ ልማት አገልግሎት ጽ/ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጋር ሆኖእያለ የደንበጫ ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በሥር ፍርድ ቤት ከተጠሪ ጋር ተከራካሪ ባልሆነበት የሰበር ቅሬታ አቅራቢ ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ተቃውመዋል፡፡ በመሆኑም የሰበር አቤቱታው በተገቢው አካል የቀረበው ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የሰበር አቤቱታው በሥር ፍርድ ቤት ተከራካሪ ባልሆነ ወገን የቀረበ በመሆኑ ተሰርዟል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ የደንበጫ ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ለተጠሪ ብር 3,000.00(ሶስት ሺ) ብር እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

- የደንበጫ ወረዳ ፍርድ ቤት የወጪ እና ኪሳራ ውሳኔውን እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ ይድረሰው ብለናል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !